
# Legacy International Spiritual Ministry 2022 GC Annual Summary Report



**Legacy International Spiritual Ministry**
**c/o P.O.Box 17979**
**Cell # 251 930 651943**
**Act: #: Berhan Bank 2600010008458; Awash Bank 013521121036500; Awash Bank 013521121036500**
**Addis Ababa, Ethiopia**

***ለዉድ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ደጋፊዎች!***

***ጉዳዩ፦* እአአ 2022 የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት ዓመታዊ ሪፖርት ባጭሩ**

ሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2017 በይፋ ሥራዉን ከጀመረ ስድስተኛ ዓመቱን አጠቃልሎ ሰባተኛዉን ተያይዟል። ስድስተኛዉን ዓመት ሲያጠቃልል በሥራ አመራር ቦርዱና በጠቅላላ ጉባዔ እአአ የ2022 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴና የኦዲት ሪፖርትን በማድመጥና በማጽደቅ ነበር። የበጎ ፈቃደኞች (በተለይ ወጣት አሠልጣኞች)፣ በጊዜያቸው፣ በዕውቀታቸውና በሀብታቸው ከአገልግሎቱ ጎን የመተደምጦቆም ሂደት አሁንም ቀጥሏል። የአገልግሎቱ አንኳር ተግባር የሆነዉ ማለትም ለሚመለከታቸዉ ተደራሾች በተለያዩ አካባቢዎች የግንባር ሥልጠናን የመስጠት ሥራ በስድስተኛዉ ዓመት ከታቀደዉ አንጻር ሲታይ የ172 በመቶ ክንዉን ዉጤት ታይቶበታል። ይህ ዉጤት ባለፉት ዓመታት ከነበሩት ዉጤቶች ሁሉ የላቀ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር ስላበዛልን ፀጋ አመስግነነዋል። ይህን ስድስተኛ ዓመት ማጠቃለያ ልዩ የሚያደርገዉ ሁለት ቴርም ያገለገሉ ቦርድ አባላት ከአገልግሎት አርፈዉ በሌሎች መተካታቸዉ ነዉ‹‹ በትዕግሥትና በትጋት ሳያቋርጡ ስድስቱን ዓመታት ስላገለገሉ ጌታ ይባርካቸዉ። የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት **ሰንበት** ላይ ስለደረስን ጌታ ይባረክ።

**ክፍል አንድ - በእግዚአብሔር መንገድ መምራት (Guidance) እአአ 2022 እሁድ አምልኮ ጨምሮ በግንባር የተሰጡ የወጣቶች፣ ወላጆችና መሪዎች/አገልጋዮች ሥልጠናዎች;**

**1.1 የወጣቶች፣ የየዕለት ግል ጥሞና ጊዜ ከጌታ ጋር ስልጠና መረታዊ ዳሰሳ ትንተናዎች**

ከሥልጠናዎች በፊት ቅድመ፣ ሲጠናቀቅ ደግሞ ድህረ ሥልጠና ዳሰሳዎች በከፊል ይካሄዱ ነበር፣ የተነተኑት የዉሰኔ ለዉጥ ዉጤት በከፊል እንደሚከተለዉ ነዉ።

በአዳማ ገንደ ሃራ (እአአ 2021) **4%፣** እአአ **2022** ኮተቤ ሲኤምሲ ሙሉ ወንጌል 21%፣ አዳማ ገንደ ጋራ ሙወ 12%፣ አምቦ ሙሉ ወንጌል 40%፣ ሙገር ሙሉ ወንጌል 21% ናቸዉ።

**1.2 የደቀ መዝሙርነትን አቅም የማጎልበት ሥራ፣ የመሪዎች፣ የወላጆች እና የወጣቶች ሥልጠና ትኩረት፤**

***ለመሪዎችና አገልጋዮች*** - የትዉልዶች ተግዳሮቶች (NWO)፣ ሎሌያዊ መሪነትና አገልጋይነት በ1ጢሞ 3:16 ላይ በመመሥረት፣ የታመነች በ/ክ ኃላፊነት (ጊዜ ሲበቃ)፣

**ለወላጆች** - የትዉልዶች ተግዳሮቶች (NWO) (በንዳንድ ጣቢያዎች) - መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ፣ - የወላጆች 7ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች - የልጆች ዕድገት ደረጃዎች (ሁለት አጥቢያ) አንዳንድ ቦታ በኢተርኔት ቪዲዮ በመደገፍ፣ አልፎ አልፎ በልጆች ድራማ በማጠናከር፣ ልጅ አስተዳደግ ዘዴዎችን ማሳየትና አዋጭ አማራጮችን መጠቀም፣

***ለወጣቶች - ወጣትነት፣ ተግዳሮቶችና መፍትሔ ሃሳቦች - በአእምሮ መንፈስ መታደስ (5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች ላይ ተመሥርቶ) - የየዕለት ግል ጥሞና ጊዜ ከጌታ ጋር - ዓላማ ያለዉ ወጣት (በአንድ ጣቢያ) - አምልኮና ልዩ የቃል ማካፈል ጊዜ***

**እሁድ አምልኮ** - ልጆችን መምከር መፀለይ፣ ለወጣቶች ትምህርትና መፀለይ፣ ለወላጆች 12 የምክር ነጥቦች ማስተላለፍ፣ አልፎ አልፎ ወንጌልም መስበክና ሀዝቡን ማጽናናት ሥራዎች ተሠርተዋል።

**1.3 *የስምጥ ሸለቆ ክልል መሠረተ* ክርስቶስ** 26 *አጥቢያዎች የተካፈሉበት ለአንድ ቀን በመሪነትና አገልጋይነት ላይ ሥልጠና በዝዋይ ላይ ወስደዋል። **ሥልጠናዉን የተካፈሉት መሪዎችና አገልጋዮች በቁጥር*** **90 ናቸዉ።**

## ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ

**ስምጥ ሸለቆ መሠረተ ክርስቶስ አገልጋዮችን በማሠልጠን ላይ**



**የስምጥ ሸለቆ ክልል መሠረተ ክርስቶስ መሪዎችና**



**⍰. ከባኮ ቁጥር አንድ ሙሉ ወንጌል ጋር**

ለሶስት ግማሽ ቀኖች የተዘጋጀ ሲሆን የተካፈሉት 175 ሲሆኑ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ በተሰጠዉ ቤተሰብ ነክ አገልግሎት መልእክቱን የሰሙት በግምት ወደ 1000 ናቸዉ። በጥቅሉ በዚህ ጣቢያ ወደ 1175 ሰዎች ተደርሰዋል።

**ባኮ ሙ.ወ. #1 ወላጆች በሥልጠና ላይ**



### 1.4 ወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር የወላጆች ብቻ ግንባር ሥልጠና

ሀ. ከጎተራ ሙሉ ወንጌል በአንድ ቀን ዉሎ የተካፈሉት ወላጆች ቁጥር 87 ናቸዉ፤ ወላጆቹ እስከ 12 ዓመት ዕድሜ ልጆች ያላቸዉ ናቸዉ፤

**ጎተራ ሠልጣኝ ወላጆች**



**ባኮ ሙ.ወ. #1 ወላጆች ሥልጠና**



**ባኮ ሠልጣኝ ወላጆች**



ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።

ሻሸመኔ ጎፋ በር ሠልጣኝ ወጣቶች



## 1.5 ከወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንባር ሥልጠና— ለወጣቶች ብቻ

ሀ. ከሻሸመኔ ጎፋ በር ሙ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር **ለሶስት ቀናት** ለወጣቶች ብቻ ሥልጠና ተሰጥቶኣል፤

በዚህ ሥልጠና ወጣቶችን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ርዕሶች የቀረቡ ሲሆን በከፍተኛዉ ቁጥር 107 ተካፍለዋል፡፡ የቦርድ ሰብሳቢ በማመቻቸትና በአሠልጣኝነት ተሳትፎ አድርጎኣል፡፡

በእሁድ አምልኮ ላይ በተሰጠዉ አገልግሎት በግምት ወደ 1000 የሚሆኑ የሌጋሲ መልእክት ሰምተዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጣቢያ በተሰጠዉ አገልግሎት በቁጥር **1107 ሰዎች** ተደርሰዋል፡፡

ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።

ሻሸመኔ ጎፋ በር ሙሉ ወንጌል ወጣት ሠልጣኞች



አዳማ ገንደ ጋራ አዳጊ/ወጣት ሠልጣኞች



አዳማ ገንደ ጋራ ወጣቶች በሥልጠና ላይ



ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።

ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።**

**ሮብ ገበያ/ጫንጮ ህይወት ብርሃን ሠልጣኝ ወላጆች**



**1.7 ከወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር-የመሪዎችና አገልጋዮች፣ ወላጆችና የወጣቶች ሙሉ ፓኬጅ ሀ. ኦለንኮሚ ሙወ ጋር-** 44 መሪዎችና አገልጋዮች፣ 63 ወላጆች፣ 80 ወጣቶች፤ በድምሩ 187 ናቸዉ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ የተገለገሉት በግምት ወደ 400 ሲሆኑ በጠቅላላ 587

**ኦለንኮሚ ሠልጣኝ መሪዎችና አገልጋዮች**



**ለ. ከኮተቤ ሲኤምሲ ሙወ ጋር፤** 39 ወላጆች፣ 26 መሪዎችና አገልጋዮች፣ 55 ወጣቶች፤ በድምሩ 120 ናቸዉ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ የተገለገሉት በግምት ወደ 350 ሲሆኑ በጠቅላላ 470 ናቸዉ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ ያገለገለቺዉ ወሮ አልጋነሽ ናት፤

**ሲ ኤም ሲ ሙወ ሠልጣኝ መሪዎችና አግልጋዮች**



**1.6 ከወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር የተሰጠ ግንባር ሥልጠና - ለወላጆችና ለመሪዎች ብቻ**

ከሮብ በገበያ/ጫንጮ ገባ ብሎ (የገጠር ከተማ) ከህይወት ብርሃን ቤ/ክ ጋር በመተባበር የ2 ቀን ሥልጠና ተሰጥቶኣል፤

በዚህ የተካፈሉት ወላጆች 40 ሲሆኑ በመሪነትና አገልጋይነት ደግሞ 33 ናቸዉ፤ መደራረብ ቢኖርም በቁጥር 73 ናቸዉ

**ሮብ ገበያ/ጫንጮ ህይወት ብርሃን ቤ/ክ መሪዎች/አገልጋዮች**



**ኦለንኮሚ ሠልጣኝ ወጣቶች**



**ኦለንኮሚ ሠልጣኝ ወላጆች**



**ኮተቤ ሲ ኤም ሲ ሙወ ሠልጣኝ ወጣቶች**



ኢየሱስ ጌታ ነዉ።

ሲ ኤም ሲ ሙወ ሠልጣኝ ወላጆች



**1.7 ሐ. ከአርሲ ነጌሌ ሙወ ጋር-** 43 መሪዎችና አገልጋዮች፣ 34 ወላጆች፣ 54 ወጣቶች፤ በድምሩ 131 ናቸዉ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ የተገለገሉት በግምት ወደ 150 ሲሆኑ በጠቅላላ 181 ናቸዉ፤

አርሲ ነጌሌ ሙ.ወ. ሠልጣኝ ወጣቶች በከፊል



አርሲ ነጌሌ ሙ.ወ. ሠልጣኝ ወጣቶች [illegible]



ቶኬ ብርሃነ ወንጌል ወላጆች በሥልጠና ላይ



ሲ ኤም ሲ ሙወ ሠልጣኝ ወጣቶች በቡድን ዉይይት ላይ



አርሲ ነጌሌ ሙ.ወ. ሠልጣኝ መሪዎች



አርሲ ነጌሌ ሙ.ወ. ሠልጣኝ ወላጆች



**1.7 መ. ከቶኬ ብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር -** 39 መሪዎችና አገልጋዮች፣ 206 ወጣቶች፤ 149 ወላጆች፣ በድምሩ 394 ናቸዉ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ የተገለገሉት በግምት ወደ 1000 ሲሆኑ በጠቅላላ 1394 ናቸዉ፤

ቶኬ ብርሃነ ወንጌል ወጣቶች በሥልጠና ላይ



**ኢ የ ሱ ስ  ጌ ታ  ነ ዉ።**



## ቶኬ ብርሃነ ወንጌል ወላጆቸ አሠልጣኝ

**1.7 ሠ. ከአምቦ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር፤** 76 መሪዎችና አገልጋዮች፣ 83 ወላጆች፣ 135 ወጣቶች፤ በድምሩ 294 ናቸዉ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ የተገለገሉት በግምት ወደ 1500 ሲሆኑ፣ በጠቅላላ 1794 ናቸዉ፤

**አምቦ ሙሉ ወ. ቁ1 ሠልጣኝ ወላጆች**



**1.7 ረ. ከሙገር ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር፤** 127 መሪዎችና አገል,ጋዮች፣ 61 ወላጆች፣ 177 ወጣቶች፤ በድምሩ 365 ናቸዉ፤ በእሁድ አምልኮ ላይ የተገለገሉት በግምት ወደ 1500 ሲሆኑ፣ በጠቅላላ 1865 ተዳራሾች ናቸዉ፤

**ሙገር ሙሉ ወ. ቁ1 ሠልጣኝ ወጣቶች**



**ቶኬ ብርሃነ ወንጌል ሠልጣኝ ወላጆች**



**አምቦ ሙሉ ወ. ቁ1 ሠልጣኝ አገልጋዮችና መሪዎች**



**አምቦ ሙሉ ወ. ቁ1 ሠልጣኝ ወጣቶች**



### 1.7 ሰ. እአአ 2022 የሁሉም ሥልጠናዎች ማጠቃለያ

በጥቅሉ በ2021 በጀት ዓመት **478** መሪዎችና አገልጋዮች፣ **920** ወጣቶች፣ በወላጅነት ሥልጠና ላይ **731** ተሳታፊዎች ሥልጠና እንደ ወሰዱ፣ በድምሩ በተለያዩ ጣቢያዎች **2129** ሠልጣኝ ተሳታፊዎች እንደነበሩና ይህ ለዓመቱ ከታቀደዉ **780** ጋር ሲነጻጸር **172%** ክንዉን ያሳያል። በዓመቱ በእሁድ አምልኮ ላይ የሌጋሲን መልእክት የሰሙ በግምት **6900** ሲሆኑ በጠቅላላዉ **9029** ሰዎች እንደተደረሱ ነዉ።

**1.8 በጎ ፈቃድ የወጣት አሠልጣኞች የተካፈሉባቸዉ** ወ/ዊ አለማየሁ ሆጤሳ 6 ኪሎ ሙወ - ኦለንኮሚ ሙወ፣ ሲኤምሲ ሙወ፣ አርሲ ነገሌ ሙወ፣ አደማ ገንደ ጋራ ሙወ፣ ሙገር (ሬጂ) ሙወ ወ/ም ጌቱ አማረ፣ ዶር ግርማ አበበ - ሻሸመኔ ጎፋ በር ሙወ፤ ፓ/ር ሳምሶን ጉታ - ቶኬ ብርሃነ ወንጌል ቤ/ከ፤ አምቦ ሙወ

**1.9 ለየት ያሉ ክስተቶች ፤** ቶኬ - ለአምልኮ ቤት ማሠሪያ ጥሪት ማሰባሰብ አገልግሎት፤ ሙገርና ቶኬ - ወንጌል ተሰብኮ ጌታን የተቀበሉ አሉ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሶስት ጣቢያዎች በግላችን መኪና ተንቀሳቅሰናል (አዳማ. አምቦ፣ ሙገር)።

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነ ዉ።**



**በወልዲያ የእዉነተኛ አምልኮ እንቅስቃሴ ጅምር**

**ክፍል ሁለት፣ ’የእዉነተኛ አምልኮ እንቅስቃሴ’ ተግባራዊነት ጅምር**

**ወልዲያ ሙሉ ወንጌል** እአአ 2021 ሙሉ ፓኬጅ ሥልጠና ተሠርቶበት የነበረ ሲሆን በኋላ በሰሜኑ ክፍል በነበረዉ ጦርነት ክልል ዉስጥ የነበረች ከተማ ናት፤ ‘Genuine Worship Initiative’ ቀደም ብሎ በተቀመጠዉ ስትራቴጂ (20፡80) ከድህነት የተነሳ ማከናወን ባይቻልም ጥቂት ባብዛኛዉ የሌጋሲ አባላትና ደጋፊ ባዋጡት (9500) እና ከሌጋሲ መጠባባቂያ ፋንድ (30500 ሺህ) በድምሩ 40 ሺህ ብር ወጪ ተደርጎ በወልዲያ ሙሉ ወንጌል አማካይነት ለ10 ተጠቃሚዎች (ተፈናቃዮችና ምስኪኖችን ጨምሮ) ሶስት ዓይነት ምግቦች (ዘይት፣ ምስር ጤፍ) ገዝቶ ማካፋፈል ተችሏል። አስሩን ግለሰቦች ጨምሮ ከነቤተሰባቸዉ የተጠቃሚዎች **ቁጥር ወደ** 30 ናቸዉ።

**ክፍል ሶስት - በማህበራዊ ሚዲያ የተከናወኑ አገልግሎቶች**

**3.1 በዌብሳይት ፌስቡክ ገጽ በሶሻል ሚዲያ እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶች (እአአ ፌብሯሪ 23፣ 2021 — ጃኑዋሪ 19፣ 2022)**

የተለያዩ የጊዜዉ ጥቅሶች የተጋሩትና በሰዎች የተጎበኙ/የተደረሱ፤ በአማርኛ 1500፣ በኦሮምፋ 343፣ በእንግሊዝኛ 189፣ በትግሪኛ 332፣ **በድምሩ 2065**፤ በእነዚሁ ላይ ተጨማሪ ሥራ የሠሩ ሰዎች **በድምሩ 102** ሲሆኑ ወድደናል ያሉት **ሰዎች 51**፣ **የሁሉ ድምር 2218** ነዉ።

**3.2 በፓ/ር ጌታቸዉ በቀለ** የተዘጋጁ 8 ክፍል የደቀመዝሙር ትምህርቶች በአማርኛ ተዘጋጅቶ እንደገና ለሌሎች ተጋርተዋል፤ የጎበኙ ሰዎች ቁጥር 512 ሲሆኑ ተጨማሪ ሥራ የሠሩ 30 ናቸዉ። ጠቅላላ ድምር 2760 ነዉ።

**ክፍል አራት - እአአ 2022 የሂሳብ እንቅስቃሴና እአአ የ2023 በጀት ዕቅድ**

እአአ 2022 (ጃኑዋሪ እስከ ዲሴምበር) ለዓመቱ ተይዞ የነበረው በጀት **591,650.00 ብር (**አምስት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ፣ ስድስት መቶ ሃምሳ ብር) የነበረ ሲሆን፣ አጠቃላይ ወጪ ብር **279,013.95** (ሁለት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ፣ አሥራ ሶስት ብር ከዘጠና አምስት ሳንቲም) ነበር፤ ይህ በኦዲቴር የተረጋገጠ ነዉ። **እአአ ለ2023 ዓም** ለአገልግሎቱ ብር 698,740.00 **በጀት** በጠቅላላ ጉባዔ ታይቶና ኃlaፊነት ለቦርዱ ተሰጥቶ ከማሻሻያ ጋር ፀድቋል።

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።**

**ማጠቃለያ** ፣ አገልግሎቱ በእግሩ እንዲቆም አገልግሎቱን በመምራት በትጋት ለተንቀሳቀሳችሁ፣ በቋሚነት ገንዘባችሁን በመለገስ ለተጋቻሁ ደጋፊዎች፣ በበጎ ፈቃደኝነት ጊዜያችሁን ፣ ጉልበታችሁን በመስጠት ላገለገላችሁ ወገኖቸ ፣ በራቸዉን በመክፈት በትብብር እየሠሩ ላሉ (አአ ዉስጥ፣ ከአአ ዉጭ ላሉ) አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወጣቶች፣ ጥልቅ ምስጋናና ዕዉቅና በዚህም ሪፖርት ተሰጥቷቸዋል።

***እርስዎና ቤተሰብዎም** ለዚህ አገልግሎት መሳካት የበኩሎዎን ድርሻ ስላበረከቱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ እንላለን።*

**መጨረሻ**